

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ. 238781

ጥር 28 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ብርሃኑ አመነው

2. በእውቀት በላይ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ብርሃኑ መንግስቱ

5. ማርታ ተካ

አመልካች፡....1. አቶ ጫኮ ጉቦ

2. አቶ ቤኮ ጉቱ

3. አቶ ጨሎ ወቼ

4. አቶ ሐጴ አዱላ

5. አቶ ጮንዴ አኖ

6. አቶ ወልዴ ኮንሴ

ተጠሪ፡..... አቶ ማጆ አጌ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የገጠር መሬት ክርክር የተጀመረዉ በደቡብ ብ/ብ/ክልል በቡርጂ ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ከሳሾች፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የደቡብ ብ/ብ/ልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.77877 ጥቅምት 25 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ



ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !



የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ፡ በቲሾ ቀበሌ ልዩ ስሙ አይጃ ተብሎ የሚጠራ አካባቢ መሆኑን ጠቅሶ አመልካቾች ተይዞብናል የሚሉትን የመሬት ይዞታ መጠን በመጥቀስ ይዞታችን በመስኖ ስናለማ የመስኖ አገልግሎት በመቋረጡ መሬቱ በማደሩ የአሁን አመልካች በ2013 ዓ.ም ከእኛ እዉቅና ወጪ የራሱ ከመሬታችን ኩታ ገጠም በመሆኑ ምክንያት በዉስጡ ገብቶ አርሶ ስለያዘ ይዞታችን እንዲለቅልን በማለት እንዲወሰልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ መልስ አመልካቾች ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ የለም፤ ሁከት እንዲወገድልን በማለት ያቀረቡት ክስ በሐሰት ነዉ፤ መሬቱን ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ ሲጠቀምበት በእጁ ያለ መሬት ነዉ፤ በዚህ ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ከአስር አመት በፊት የተሰጠኝ በእጁ ያለ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት፣ የሰዉ ምስክሮችን በመስማት እና የሰነድ ማስረጃ በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ በጠቀሰዉ ቦታ ያለዉ መሬት መጠን 0.5 ሄክታር ሆኖ ሳለ አሁን የያዘዉ 1.2350 በመሆኑ እና ከአመልካቾች ይዞታ ጋር ኩታ በመሆኑ የአመልካቾችን መሬት አልፎ መያዙ ስለተረጋገጠ፣ ተጠሪ የአመልካቾችን ይዞታ አልፎ የያዘዉን መሬት ሙሉ ለሙሉ እንዲለቅ ወስኗል፡፡ የቡርጂ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ብ/ብ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ አሁንም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለደቡብ ብ/ብ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ በዚህ ቦታ ስፋቱ 1.2530 የሆነዉ ይዞታ በስሙ ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑንና በሶያማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በስሙ ጊዜያዊ አልሚነት ማስረጃ ተሰጥቶት እያለ ይህ ማስረጃ በስህተትና በተጭበረበረ መንገድ ለተጠሪ ተሰጥቷል የሚል ወገን በሕጋዊ መንገድና በሥርዓቱን ተከትሎ እንዲስተካከል ከሚመለከተዉ አካል አቤቱታ ባላቀረበበት፣ ለፍ/ቤት በተሰጠዉ ማብራሪያ መነሻ ብቻ ማዘጋጃ ቤቱ ቀደም ሲል የተሰጠዉ ማስረጃ ባለሙያን በማሳሳት የወሰደ በመሆኑ አምክኗል በማለት የሰጠዉን መግለጫ እንዳለ ተቀብሎ የአሁን ተጠሪ ለረጅም ጊዜያት በእጁ አድርጎ በመያዝ የመንግስት ግብር በመክፈልና ለይዞታዉ ሕጋዊ የባለይዞታነት ማስረጃ በስሙ በማስመዝገብ ባለመብት መሆኑን የሚያመለክት ስለሆነ ጊዜያዊ የእርሻ ይዞታ ሠርቲፍኬት የሶያማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በስሙ መዝግቦ ማስረጃ ሰጥቶት እያለ ይዞታዉን ለአሁን አመልካቾች እንዲለቁ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፣ የአሁን ተጠሪ የአመልካቾችን ይዞታ አልያዘም፣ ይዞታዉን ለአሁን አመልካቾች ሊለቅላቸዉ አይገባም በማለት የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካቾች በ3/4/2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ተጠሪ ለክርክር መነሻ የሆነዉን ይዞታችንን ዘልቆ የገባዉ በ2013 ዓ.ም እንጂ ለረጅም አመት የተጠቀመዉ አይደለም፤ ተጠሪ ከእኛ ጋር በኩታ ገጠም ያለዉ ይዞታ 0.5 መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ከሶያማ ማዘጋጃ ቤት የተሰጠዉ

ጊዜያዊ መጠቀሚያ የምሰክር ወረቀት ላይ መጠኑ 1.2530 የተጠቀሰ ቢሆንም ተጠሪ ይህን ማስረጃ ያወጣዉ ማዘጋጃ ቤቱን በማሳሳት መሆኑን አረጋግጦ አምክኗል። ተጠሪ ያለዉ ይዞታ 0.5 ሄክታር ብቻ ነዉ። ለተጠሪ የተሰጠዉ ማስረጃ ከደንብ ዉጭ የተሰጠዉ መሆኑ ተረጋግጦ ሊሰረዝ ችሏል። የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የማስረጃ ምዘና መርህን በሚጻረር መልኩ የቀረቡትን ማስረጃዎች በአግባቡ ሳይመዝን የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን። ተጠሪ ያነሳዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያም አልነበረም። በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን፤ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች እንዲጸኑልን በማለት አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በዚህ ጉዳይ የክልሉ ሰበር ችሎት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠዉን ዉሳኔ የሻረዉ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም ተጨማሪ ማጣሪያ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ26/7/2015 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት ባጭሩ፡ የሥር የክልሉ ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር በአግባቡ መርምሮ የሰጠዉ ዉሳኔ የህግ ስህተት የሌለዉ ስለሆነ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካቾች በ7/9/2015 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር እና ለቅሬታዉ መነሻ የሆነዉን ዉሳኔ አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ የአመልካቾች እና የተጠሪ ይዞታ ኩታ ገጠም በመሆኑ አመልካች በ2013 ዓ.ም ይዞታችን ዉስጥ ገብቶ ስለያዘብን እንዲለቅልን በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ፣ ተጠሪ በበኩሉ የአመልካቾችን ይዞታ አልያዝኩኝም ይዞታዉ በእጄ ያለና የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠኝ ነዉ በማለት ተከራክሯል። የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰዉ ምስክሮችን በመስማት፣ ከሶያማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ እና የቀረበዉን የሰነድ ማስረጃ በመመርመርና በመመዘን በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ የተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በ0.5 ሄክታር መሬት ላይ ሲሆን ከሶያማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ደግሞ ስፋቱ 1.2530 ላይ ጊዜያዊ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጠዉ መሆኑንና ይህ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በተጭበርበረ መንገድ የግለሰቦችና የመንግስት መሬት ላይ የተሰጠዉ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰረዘ መሆኑ ስለተረጋገጠ፣ የተጠሪ ይዞታ ከአመልካቾች ይዞታ ጋር ኩታ ገጠም በመሆኑ በዚህ ምክንያት የአመልካቾች ይዞታ ዉስጥ ገብቶ የያዘባቸዉ መሆኑ ስለተረጋገጠ እንዲለቅላቸዉ መወሰኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል። የሥር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ዉሳኔ በማጽናት መወሰኑን መዝገቡ ያሳያል። በመሆኑም የወረዳዉ ፍ/ቤት እና በየደረጃዉ ያሉት ፍ/ቤቶች ፍሬ ነገር ለማጣራትና ማስረጃ መርምሮና መዝኖ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ በሕግ በተሰጣቸዉ ስልጣን መሰረት ተጠሪ የአመልካቾችን ይዞታ አልፎ መያዙን በማረጋገጥ ይህን ይዞታ ለአመልካቾች እንዲለቅላቸዉ መወሰናቸዉን መገንዘብ ይቻላል።

እንደሚታወቀዉ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3) (ሀ) እና በክልሉ የፍ/ቤቶች አዋጅ መሰረት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በክልል ጉዳዮች ላይ የተሰጡትን የመጨረሻ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ እንደሆነ የማረም ስልጣን እንዳለዉ ያስገነዝባል፡፡ ነገር ግን የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ የህግ ድንጋጌ ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ መርምሮ መዝኖ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የለዉም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.184787፣ 186186 እና በተለያዩ መዛግብት ላይ በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ዉሳኔ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት እና በፍ/ቤቶቹ ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት የተሰጠዉ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የመጨረሻ ዉሳኔ ባገኙ የክልል ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ በሰበር ከማረም ባለፈ ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ መርምሮና መዝኖ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ስልጣን እንዳልተሰጣቸዉ መወሰኑን ማየት ይቻላል፡፡ ይህ አስገዳጅ የሰበር ችሎት ዉሳኔ በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ማለት ነዉ፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ስንመለስ የክልል ሰበር ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች ፍሬ ነገር ለማጣራትና ማስረጃ መርምሮና መዝኖ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ በሕግ ስልጣን በተሰጣቸዉ አግባብ የግራ ቀኙን ክርክር ከግራ ቀኙ ማስረጃ እና ከሚመለከተዉ የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት ተጣርቶ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ማስረጃዉን መርምሮና መዝኖ ተጠሪ የአመልካቾችን ይዞታ አልፎ የያዘ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ በማረጋገጥ ድምዳሜ ላይ የደረሱ በመሆኑ፣ ይህን የሥር ፍ/ቤቶችን የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ የክልሉ ሰበር ችሎት ከመቀበል በስተቀር ፍሬ ነገር ድጋሚ የማጣራትና ማስረጃ መርምሮና መዝኖ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ በሕግ ስልጣን አልተጠዉም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች ማስረጃን መርምሮና መዝኖ በፍሬ ነገር ደረጃ ድምዳሜ የደረሱበትን ፍሬ ነገር መቀበል ሲገባዉ ማስረጃ መርምሮና መዝኖ የሶያማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት መክኗል ያለዉን ማስረጃ አልመከነም እንዲሁም ተጠሪ የአመልካቾችን ይዞታ አልፎ ይዟል ተብሎ ድምዳሜ ላይ የደረሱበትን ተጠሪ የአመልካቾችን ይዞታ አልያዘም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ከስልጣኑ ውጭ የህግ መሰረት የሌለዉ ዉሳኔ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ ሰበር ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን ተጠሪ የአመልካቾችን ይዞታ አልፎ መያዙን አረጋግጦ ዉሳኔ ሰጥቶ እያሉ ከስልጣኑ ውጭ የተጠሪ የተሰረዘዉን ጊዜያዊ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር መሰረት በማድረግ ተጠሪ የአመልካቾችን ይዞታ አልፎ አልያዘም በማለት ከስልጣኑ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የደቡብ ብ/ብ/ልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.77877 ጥቅምት 25 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ስለሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የቡርጂ ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.13849/2014 በ30/7/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የቡርጂ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.058227 በ18/8/2014 የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የደቡብ ብ/ብ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.77775 በ28/12/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

መ/ዐ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**